# የቼሪ ክሪክ ቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት

## የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት

## **ለወላጆች የተዘጋጀ መመሪያ**

ለወላጆች በተዘጋጀ የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት መመሪያ ውስጥ በፍደላት ቅደም ተከተል መሰረት የተካተቱት መረጃዎች በሙሉ የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት ድጎማ/ድጋፍ የሚያገኙትን ወላጆች የሚመለከት ሲሆን፣ ቀጥሎ ያሉትን ሁኔታዎች ያካትታል፤

**ገንዘብ መሰብሰብ**

ለማንኛውም ትምህርተ-ነክ አገልግሎቶች (የመስክ ጉብኝት፣ ፎቶ፣ ወዘተ.) ክፊያ የሚያስፈልግ ከሆነ አስተማሪ ያሉትን የገንዘብ ድጎማ አማራጮች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት ወላጆች ያሳውቃል።

**ምዝገባ**

ክፍል 4-አንድ ልጅ የሚፈለገውን የዕድሜ ገደብ ከደረሰና የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት ድጎማ የሚያገኝ ከሆነ፣ መጸዳጃ ቤት ሄዶ መጸዳዳት ስለማይችል ብቻ ለዚህ የትምህርት ዕድል ምዝገባ አይከለከልም።

የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት ድጎማ/ድጋፍ የሚያገኙ ወላጆች የመመዝገቢያና ወርሃዊ የትምህርት አገልግሎት ክፊያ አይከፍሉም።

**ቅጾች**

የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት ወላጆች የትምህርት አገልግሎት ክፊያ ስምምነት ቅጽ አይሞሉም፤ ከዚህ በተረፈ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቅጾች ሁሉ የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት ወላጆችን ይመለከታቸዋል፤

- የኮሎራዶ ክፍለ-ግዛት የክትባት ማረጋገጫ የሰርትፍከት ወረቀት። ይህ ካልተሟላ ልጁ ከመጀመሪያ የትምህርት ቀን ጀምሮ የመማሪያ ክፍል እንዳይገባ ሊከለከል ይችላል።
- የቼሪ ክሪክ ትምህርት ቤቶች በድንገተኛ ጊዜ የሚደወልበት የስልክና የስም መረጃ የሚመዘገብበት ካርድ ከመጀመሪያው የትምህርት ቀን ጀምሮ መሟላት አለበት።
- የልጅ የጤና ሁኔታ የሚገልጽ ቅጽ ከመጀመሪያ የትምህርት ቀን ጀምሮ መሟላት አለበት።
- የተማሪ ጠቅላላ መረጃ ቅጽ
- የተማሪ መረጃን ወደ የመማሪያ ክፍል የማስተላለፍ ቅጽ
- የተማሪ ለትምህርተ-ነክ ጉዳዮች ፎቶ መነሳት ወይም ቪድዮ መቀረጽ ፈቃድ ቅጽ
- በተጨማሪም፣ የድስትሪክት ገንዘብ-ነክ ጉዳዮች ቅጽ

**የወላጅ ተሳትፎ**

በዚህ መመሪያ ውስጥ ከተካተቱት ሃሳቦች በተጨማሪ፣ የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት የሚያገኙት ልጆች ወላጆች በትምህርት ማዕከሉ ኮሚቴና በድስትሪክት የቅድመ-መዋዕለ-ህጻናት ትምህርት አገልግሎት የወላጅ ፖሊሲ ኮሚቴ ውስጥ እንዲሳተፉ በጣም ይበረታታሉ። የእነዚህን ኮሚቴዎች መረጃ ከፈለጉ የወላጆች አገልግሎት ክፍልን ያነጋግሩ።